## በዩንቨርሲቲዉ ዉስጥ የሚፈፀም ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል የወጣ
## *መመሪያ*

በኢፌዴሪ ህገ መንግስትና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች መሠረት ማንኛውም ሰው በነፃነት የመማር፤ መልካምና ምቹ የመማሪያ አካባቢ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣

የወሲባዊ ትንኮሳ ተግባር በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ተግባር ቢሆንም፣ በተለይ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑት ሴቶች በመሆናቸው ትምህርታቸውን ከወንዶች እኩል በመከታተል ውጤታማ እንዳይሆኑና ሀገራዊ ኃላፊነታቸውንም እንዳይወጡ እንቅፋት እየሆነባቸው በመምጣቱ፣

ወሲባዊ ትንኮሳ የሰብአዊ መብት ጥሰት በመሆኑ፤ በተለይም በትምህርት ተቋማት አካባቢ እየተፈፀመ ያለው የወሲባዊ ትንኮሳ ተግባር ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዳይኖር እንቅፋት እየሆነ በመምጣቱና በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ብቃትና ውጤታማነት የሚያቀጭጭ በመሆኑ፣

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየተፈፀሙ ያሉ ወሲባዊ ትንኮሳ ተግባራትን ለመከላከል፣ ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት እንዲሁም የጥፋት ድርጊት ፈፃሚዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 97(2) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ወሲባዊ ትንኮሳ"** ማለት ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ በሌላ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ ከሌላኛው ፈቃድ ውጪ ወይም ወሲባዊ ጥያቄን እንደ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ( Quid Pro Quo) የሚቀርብ የወሲብ ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ይዘት ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪ ተግባር ይሆናል፡፡

# አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ

## ሀ) <u>ቀላል የወሲብ ትንኮሳ ዓይነቶች፣</u>

1. አስነዋሪ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ አካላትን አጋልጦ ማሳየት፣
2. የሌላውን ወሲባዊ ፍላጐት ሊያነሳሱ የሚችሉ ፅሁፎችና መጽሔቶችን በዩንቨርሲቲ ውስጥ ለሌሎች ማሳየት፣
3. .ወሲብ አዘል ሁኔታን የሚያንፀባርቁ ቀልዶች፣ ቧልቶች፣ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎች፣ ገጠመኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ ፈፅሞ መገኘት/መናገር/፣
4. ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ጾታን ማጥላላት፣ ማናናቅና ማንኳሰስ፣
5. በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ለምሳሌ በሞባይልና በመሳሰሉት የወሲብ ምስል፤ የፁሁፍ መልእክት እና ፎቶ ግራፍ ያለአንዱ ወገን ፈቃድ ለሌላ ሰው ማሳየት ወይም ማስተላለፍ፣
6. ለወሲብ በሚያነሳሳ መልኩ የአካል እንቅስቃሴ ለሌላ ወገን ማሳየት፣
7. የአንድ ሰው ፆታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስ የተመለከቱና ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው አስተያየቶች፣ ነቀፌታዎች፣ ያልተፈለጉና አዋራጅ መገለጫዎችን፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን መጠቀም፣
8. ተግባር ተኮር ትምህርቶች በሚሰጥበት ወቅት ወሲባዊ ድርጊትን በሚያመላክት መልኩ የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ወይም የቃል አስተያየቶችን መስጠት፣

*አድራሻ፡- አዲሱ አስተዳደር ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 408*

*☏ 022 211 04 61*

## ለተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው

1. አዲስ የሚገቡ ሴት ተማሪዎች መልካም ተሞክሮ ባላቸውና በህብረተሰቡ ዘንድ አርአያ በሆኑ ሴት መምህራን፣ሴት አስተዳደር ሰራተኞና ሴት ተማሪዎች አማካኝነት ተሞክሮን ማካፈል
2. በዩኒቨርስቲው በተለያየ መልክ በሴት መምህራን ፣ሴት አስተዳደር ሠራተኞችና ሴት ተማሪዎች ላይ የሚደርሰውን ዘርፈ፣ብዙ የሆኑትን፣ፆታዊ ጥቃቶችን መከላከልና መቆጣጠር
3. ለአንደኛ አመት ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎትና የስነ-ተዋልዶ ጤና ስልጠና መስጠት
4. በዩኒቨርስቲው ከሁሉም ት/ቤቶች በትምህርታቸው ከፍትኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ሴት ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት መስጠት
5. በዩኒቨርስቲው የኢኮኖሚ ድጋፍ ለሚሹ ሴት ተማሪዎች የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ
6. ለዩኒቨርስቲው ሴት መምህራንና ሴተ አስተዳደር ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና፣መስጠት
7. ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በተመረጡ ኮርሶች ላይ የማጠናከሪያ ትምህርት (Tutorial class) መስጠት
8. ፍላጎት ላላቸው ሴት ተማሪዎች የኮምፒውተርና የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ስልጠና መስጠት
9. በአዳማ ከተማ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤቶች በሣይንስና ሂሳብ ትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት ለሚያስመዘግቡና በፈጠራ ስራቸው እውቅና ለአገኙት ሴት ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት መስጠት
10. በዩኒቨርስቲው በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ በመሰማራት ከፍተኛ ውጤት ለሚስመዘግቡ ለምስጉን ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት መስጠት
11. የምክር አገልግሎት ( counseling service ) መስጠት

## <u>ለ) ከባድ የወሲብ ትንኮሳ ዓይነቶች፣</u>

9. በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ፣ በድህረ ገፅ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛን ምስል በመጠቀምና በማስመሰል የሌላን ሰው ወሲባዊ ሕይወት የሚያጋልጡና የሚያንቋሽሹ ተግባራትን መፈጸም፡፡

10. አንድን ሰው በማንኛውም ቦታ በመከታተል እና በነፃነት የመንቀሳቀስ መብትን በመጋፋት ላይ የስነልቦና ጫና ማሳደር፣

11. ለትምህርት ውጤት ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ አስቀምጦ መጠየቅ፣

12. ወሲብ አዘል ድርጊቶችን በማስገደድ ለመፈፀም በማሰብ የትምህርት መሣሪያዎችና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማትና መደበቅ፣

13. ቀላል የወሲብ ትንኮሳ በመፈፀም በተወሰደበት የቅጣት እርምጃ ባለመታረም በተደጋጋሚ ቀላል የወሲብ ትንኮሳዎችን መፈፀም፣

14. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ቀላልና ከባድ የወሲባዊ ትንኮሳ አይነቶች እንዲፈጸም የተባበረ ወይም ያደመ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ እንደጥፋቱ ድርጊት እርምጃዎች ሊወሰዱበት ይችላል፡፡

15. በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም ቀላል ወሲባዊ ትንኮሳ በከባድ የወሲባዊ ትንኮሳ ተግባራት ከተመለከቱት የጥፋት ድርጊቶች ጋር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል፡፡

**"ፆታዊ ጥቃት ይቁም"**

## በጥቃት አድራሾች ላይ የሚወሰዱ

## የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች

ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን የወሲባዊ ትንኮሳ አይነቶች ከፈጸመ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት የቅጣት አይነቶች አንዱ ተፈጻሚ ይደረግበታል፡፡

**በተማሪዎች ላይ የሚወሰድ ቀላል የሥነ ሥርዓት እርምጃ፣**

ሀ· ተግሳፅ/የቃል ማስጠንቀቂያ፣
ለ· የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
ሐ· የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

**በተማሪዎች ላይ የሚወሰድ ከባድ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣**

ሀ· ለአንድ ሴሚስተር ከትምህርት መታገድ፣
ለ· ለአንድ አመት ከትምህርት መታገድ፣
ሐ· ተመራቂ ተማሪ ሲሆን የትምህርት ማስረጃን እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ማገድ፣

**በዩንቨርሲቲዉ መምህራን ላይ የሚወሰድ ቀላል የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣**

ሀ· ተግሳፅ/የቃል ማስጠንቀቂያ፣
ለ· የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
ሐ· እስከ 2 ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፣

4. **በዩንቨርሲቲዉ መምህራን ላይ የሚወሰድ ከባድ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣**

ሀ. የሦስት ወር ደመወዝ መቀጮ፣
ለ.. ካለበት የደመወዝ ደረጃ እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ፣
ሐ· ከሥራ ማሰናበት፣

### በዩንቨርሲቲዉ ሴት ተማሪዎች ፣ ሴት መምህራን፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ላይ ፆታዊ ጥቃት በሚፈፅሙ ሠዎች ላይ የሚወሰድ የሥነ-ሥርዓት እርምጃን በተመለከተ

በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 67 መሠረት የተቀመጡ የቅጣት አይነቶች በዲስፒሊን ኮሚቴ ተጣርቶ በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት በኘሬዝዳንቱ ይወሰናል፡፡

**ሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ፣**

ዩንቨርሲቲዉ በተማሪ፣ በመምህራኖችና በድጋፍ ሠጪ ሠራተኞች ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ትንኮሣን አጣርቶ የውሣኔ ሃሣብ ለኘሬዚዳንት የሚያቀርብ የወሲባዊ ትንኮሣ አጣሪ ኮሚቴ አለዉ፡፡

**የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፣**

- ማንኛውም የወሲባዊ ትንኮሣ ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ጉዳዩ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ **<u>በ30 ቀናት</u>** ውስጥ ለከፍተኛ ተቋሙ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ ከሆነ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡
- የአቤቱታ ማመልከቻ መያዝ ስለሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦች፣

ሀ. የከሳሽ ስምና ፊርማ
ለ. የሚማመርበት ት/ ክፍል ወይም የሚሰራበት ክፍል
ሐ. ድርጊቱ የተፈፀበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት
መ. ተፈፀመ የተባለው የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነት/የድርጊቶ መገለጫዎች
ሠ. የሚታወቅ ከሆነ የትንኮሳው ፈፃሚ ስምና የትምህርት ክፍል/የሥራ ቦታ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ
ረ. የምስክሮች ስም
ሰ. በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ
ሸ. የሚጠየቅ ዳኝነት
ቀ. የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበት ቀን መያዝ ይኖርበታል፡፡